# ቅይጥ አቅርቦት እንዲሁም የካፒታል ግንባታ ሲከናወን የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 20/2001

የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢዎች በአዋጁ አንቀጽ 21(2) መሠረት ወደ አገር ባስገቧቸውና በአገር ውስጥ በገዟቸው ዕቃዎች ላይ የከፈሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ መደረግ ስለሚገባው፣

ከታክስ ማቀናነስ ወይንም ማካካስ ጋር በተያያዘ በከፊል ከታክስ ነፃ እንዲሁም ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት የዋለ ጥሬ ዕቃ ላይ የተከፈለ ታክስ የሚካካስበትን ስሌት ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

አንድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የካፒታል ማስፋፋት ስራዎች በሚያከናውንበት ጊዜ በግንባታ ሂደት የተከፈለ የግብዓት ታክስ እንዴትና መቼ መቀናነስ እንዳለበት መወሰን በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1995 አንቀጽ 27 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ቅይጥ አቅርቦት እንዲሁም የካፒታል ግንባታ ሲከናወን የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ የወጣ መመሪያ ቁጥር 20/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ:-
   1) "ታክስ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡
   2) "አዋጅ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ነው፡፡
   3) "ሰው" ማለት የተፈጥሮና የሕግ ሰው ነው፡፡
   4) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡

3. <u>የታክስ አቀናነስ</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 21(2) መሠረት ወደ አገር በገቡ እና በአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎች የታክስ ተቀናሽ ወይም ማካካስ ተፈፃሚ የሚሆነው በቀጥታ ከሥራው ወይም ከአቅርቦቱ ጋር ግንኙነት ባለው ግብዓት ላይ ብቻ ነው፡፡
2. ከታክስ ነፃ ለሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደ አገር ውስጥ በገቡ ወይም ከአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ የተከፈለ ታክስ ተቀናሽ አይደረግም፡፡
3. ለአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) (ሐ) አፈፃፀም በከፊል ታክስ ለሚከፈልበትና በከፊል ከታክሱ ነፃ ለሆኑ ግብይቶች በዋሉ ወደ አገር በገቡና ከአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የተከፈለን ታክስ የተመዘገበው ሰው ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሰረት አስልቶ ማቅረብ አለበት፡፡

| ተ = ሀ X ለ/ሐ |
|---|

ለዚህ ስሌት አፈፃፀም፡-

ተ= ታክስ/ክሬዲት ሊደረግ የሚገባ የተከፈለ ታክስ፣

ሀ= በከፊል ታክስ በሚከፈልበት በከፊል ደግሞ ከታክሱ ነፃ በሆነ ግዢ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣

ለ= የተመዘገበ ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ፣

ሐ= የተመዘገበው ሰው በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ያከናወነው ጠቅላላ ግብይት፣

ተደርገው ተወስደዋል፡፡

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ/ሐ) መሠረት የሚገኘው ውጤት ከ0.90 በላይ ከሆነ የተመዘገበው ሰው በአዋጁ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ (2) "ሐ" በተመለከተው መሠረት በአገር ውስጥ በገዛቸው ወይም ከውጭ አገር ባስገባቸው ዕቃዎች ላይ የከፈለው ታክስ ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

4. <u>ተመላሽ ታክስን በሌላ ሁኔታ ስለማስላት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2(3) በተመለከተው መሠረት ማስላት ካልተቻለና የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት እና ከታክሱ ነፃ የሆነ ግብይት የሚያካሂድ ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ ተቀናሽ የሚደረገውን ታክስ ተገቢ መስሎ በታየው ሌላ ስሌት እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል።

5. <u>ከካፒታል ማስፋፋት ጋር ተያይዞ ስለሚደረግ የታክስ ተቀናሽ፤</u>

1. አንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ሰው የንግድ ሥራውን በማስፋፋት ሂደት በመገንባት ላይ ባሉ ህንፃዎች ወይንም ሌሎች ካፒታሎች ላይ የተከፈለን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ከሌላ ታክስ ከሚከፈልበት ዘርፍ ከተሰበሰበ ታክስ ላይ እንዲያቀናንስ አይፈቀድለትም።
2. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 (1) የተገለፀው ቢኖርም በመገንባት ላይ ያለው ህንፃ ወይንም ሌላ ካፒታል ተጠናቆ ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ተግባር መዋሉ ሲረጋገጥ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ተግባር ለማጠናከር ሲውል በግብዓቱ ላይ የተከፈለውን ታክስ ስራ ሲጀምርና ገቢ ሲያመነጭ ከሚሰበሰበው ታክስ ላይ ማቀናነስ ይቻላል።
3. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አፈፃፀም የግብዓት ታክሱ የማስታወቂያ ጊዜ ካፒታሉ ታክስ የሚከፈልበትን ገቢ ማመንጨት ከጀመረበት ወር ጀምሮ ይሆናል።
4. ለሕንፃው ግንባታ ለሥራ ተቋራጭ የተከፈለው የግብዓት ታክስ ተመላሽ የሚሆነው ተቋራጩ ሕጋዊ ፍቃድ ያለው ሲሆንና ተቋራጩ በሚያቀርበው የግብዓት ዋጋ ዝርዝር(Bill of quantity) መሠረት በተከፈለና በተረጋገጠ ታክስ መጠን ነው።
5. የተመዘገበ ሰው የተከፈለ ታክስ ሳይቀነስለት የካፒታሉ አካል ሆኖ እንዲታሰብለት ከፈለገ ዓመታዊ የአገልግሎት ዋጋውን በማስላት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 23 መሠረት በንግድ ሥራ ሀብቶች የእርጅና ቅናሽ ሥርዓት ማቀናነስ ይችላል።

# የግብር/ታክስና ቀረጥ ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት ስለሚሰጥ የምስክር ወረቀት /ክሊራንስ/ አሰጣጥ መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# የግብር ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት ስለሚሰጥ
# የምስክር ወረቀት /ክሊራንስ/
# አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 19/2001

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ገቢ ተገቢውን የግብር/ታክስ ገቢ በመሰብሰብ ሂደት ለግብር ከፋዩ የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጥ በመሆኑ፣

ከነዚህም አገልግሎቶች መካከል የባለሥልጣኑ ግብር ከፋዮች የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ፣ በጨረታ ለመሳተፍ፣ የተሽከርካሪ ደህንነት ምርመራ ለማድረግ፣ የንብረት ባለቤትነት ለማዛወር፣ የንግድ ሥራ ሲያቋርጡም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ለማግኘት በአገልግሎት ሰጪዎች ከሚጠየቁ ማስረጃዎች አንዱ በባለሥልጣኑ የሚሰጠው የግብር/ታክስ/ ቀረጥ ዕዳ አከፋፈል ምስክር ወረቀት በመሆኑ፣

የምስክር ወረቀት መስጠቱም የገቢ አሰባሰቡን ውጤታማ በማድረግ ረገድ የራሱ ድርሻ ያለው በመሆኑና ይህም ወጥ በሆነ ስርዓት መመራት ስላለበት፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚኒስትሮች ም/ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 27 እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1994 አንቀጽ 39፣ እንዲሁም በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 112(2)፣ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀጽ 55፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 አንቀጽ 38፣ እና በቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 አንቀጽ 14 ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የግብር/ታክስና ቀረጥ አከፋፈል ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት ስለሚሰጥ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 19/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) "የምስክር ወረቀት /ክሊራንስ/" ማለት አንድ ግብር ከፋይ የግብር/ታክስና ቀረጥ ክፍያ ግዴታውን የተወጣ ወይም በተለያየ ሁኔታ በመወጣት ላይ፣ ወይም አንድን ግዴታ ብቻ የተወጣ ለመሆኑ የሚሰጥ የጽሑፍ ማረጋገጫ ነው።
2) "ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች" ማለት እንደ ጎርፍ፣ ቃጠሎ፣ በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ ዝርፊያ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ የመሳሰሉ የተፈጥሮና ግብር/ታክስ ከፋዩ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ ሰው ሰራሽ ችግሮችን ያካትታል።
3) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

## 3. የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች

ባለሥልጣኑ የግብር ግዴታውን ለተወጣ እና በመወጣት ላይ ለሚገኝ ግብር፣ ታክስና ቀረጥ ከፋይ በግብር ከፋዩ በሚቀርብ ጥያቄ መነሻነት ቀጥሎ ለተመለከቱት ጉዳዮች ማስፈጸሚያ የምስክር ወረቀት /ክሊራንስ/ ይሰጣል፣

1) የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ፣
2) በጨረታ ለመካፈል /ለመሳተፍ፣
3) ለተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ከላውዶ፣
4) ተሽከርካሪ ለመሸጥ፣ ስም ለማዛወር፣ የሰሌዳ ለውጥ ለማድረግና የመድን ካሳ ለማግኘት፣
5) ከንግድ ጋር የተያያዘ የመኖሪያና የንግድ ቤት ለመሸጥ፣ የድርጅት ስም ለመለወጥ ወይም ድርጅት ለመዝጋት፣ ወይም የአክሲዮን ባለቤትነት መብት ለማዛዋወር፣

6) በሰስተኛ ወገን ስለ ግብር፣ ታክስና ቀረጥ ከፋዩ እንዲሁም ስለወጪ መጋራት ክፍያ መረጃ ሲጠየቅ፣

7) ለወጪ ንግድ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የቫውቸር እድሳት ለማድረግ፣ እና

8) በሌሎችም በቂ ምክንያቶች፣

## 4. የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

1) የሚከተሉት ከተሟሉ የምስክር ወረቀት በቀጥታ ሊሰጥ ይችላል፤

ሀ/ ግብር/ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብርና ታክስ የከፈለ ወይም ውዝፍ የግብር/ታክስ እዳ የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ/ ግብር ከፋዩ ያለበትን የግብር፣ ታክስና ቀረጥ እዳ በወቅቱ ከፍሎ ያጠናቀቀ ከሆነ ወይም በተወሰነ ጊዜ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ስምምነት የገባ ከሆነና በስምምነቱ መሠረት ግዴታውን እየተወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ ግብር/ታክስ ከፋዩ በተጠየቀው የግብር/ታክስ እዳ ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ፣ ወይም ለግብር ይግባኝ ጉባኤ፣ ወይም ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ ከሆነ፣

መ/ በግብር ዘመን እና/ወይም በሂሣብ ጊዜው ባስታወቀው መሠት የግብር እና የታክስ ግዴታውን ከተወጣና ውዝፍ ዕዳ የሌለበት ከሆነ፣

ሠ/ በባለሥልጣኑ ወይም በሌላ በሚመለከተው አካል በተለየ ሁኔታ ግብር ከፋዩ ከግብር፣ ታክስና ቀረጥ ነፃ መብት እና ወይም የግብር እፎይታ ጊዜ ላይ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ረ/ ግብር ከፋዩ ከአቅም በላይ የሆነ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግር/አደጋ አጋጥሞት የግብር ክፍያ ግዴታው በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ በአስተዳደራዊ መልኩ ታይቶ ሲወሰን፣

2) የሚከተሉት እስከሚጣሩ የምስክር ወረቀት ወዲያውኑ ሊስተናገድ/ሊሰጥ አይችልም፡-

ሀ/ ግብር ከፋዩ በተመዘገበበት የንግድ ፈቃድ ምንም ዓይነት ሥራ አለመስራቱ እስከሚረጋገጥ፣

ለ/ ግብር ከፋዩ በደረሰው የግብር/ታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ ላይ አቤቱታ /ይግባኝ/ አቅርቦ ጉዳዩ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወይም በግብር ይግባኝ ሰሚ

ጉባኤ ወይም በፍርድ ቤት የተያዘ ከሆነና ሌላ ውዝፍም ሆነ የዘመኑ የግብር፣ ታክስና ቀረጥ እዳ የሌለበት መሆኑ እስከሚረጋገጥ፣

## 5. የምስክር ወረቀት የማይሰጥባቸው ሁኔታዎች/ምክንያቶች

1) ጠያቂው ግብር ከፋይ ከላይ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) ላይ የተገለፁትን ቅድመ ሁኔታዎች ሳያሟላ ሲቀር፣
2) የግብር ከፋዩን የታክስ እዳ ለማወቅ ኦዲት ማድረግ በማስፈለጉ ምክንያት የኦዲት ውጤት ታውቆ የሚፈለግ ታክስ እስኪከፈል ድረስ ክሊራንስ የማይሰጥ ሆኖ ኦዲት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፡፡
   ሀ/ የጠያቂው ግብር ከፋይ ድርጅት የተጣራ ሃብት እና ወይም በሂሣብ መግለጫው ከተመዘገበ ቋሚ ንብረቱ ከ50 በመቶ በላይ የሚሸጥ ከሆነ፣
   ለ/ ድርጅቱን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት ከሆነ፣
   ሐ/ የአክሲዮን ወይም ንብረት ዝውውር ጥያቄ ከሆነ፣
   መ/ የነበረውን ሕጋዊ ስያሜ በሌላ ስም ለመቀየር ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፣
   ሠ/ የተለያዩ ሕጋዊ ሕልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ የመደራጀት ወይም የመዋሃድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣
3) ጠያቂው ግብር ከፋይ የግብር፣ የታክስና ቀረጥ ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር፤
4) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 73(3) መሠረት ጥፋተኛ የሆነ ግብር/ታክስ ከፋይ ሆኖ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ካልተሰጠው፣
5) በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 81 መሠረት የግብር አወሳሰን ሊያደናቅፍ የሚችል ሁኔታ ኖሮ የግብር ከፋዩ የባንክ ሂሣብ ከታገደና የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወጥቶ የግብር አወሳሰኑ ካልተጠናቀቀ፣
6) ከዚህ በላይ በተመለቱት ሁኔታዎች የምስክር ወረቀት ካልተሰጠ ለግብር/ታክስ ከፋዩ ምክንያቱ በጽሑፍ ሊገለጽለት ይገባል፡፡

## 6. የምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት ሊጣሩ የሚገባቸው ጉዳዮች

ባለሥልጣኑ የምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት የሚከተሉትን ማጣራት ይኖርበታል፡-

1) ከግብር ከፋይ የሚፈለግ ማናቸውም ወርሃዊ ወይም ዓመታዊ ግብር ማሳወቂያዎችን በወቅቱ ማቅረቡና የሚፈለግበትን ውዝፍ የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርንር ኦቨር ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ የደመወዝ ገቢ ግብር፣ የቴምብር ቀረጥ እዳ ወይም ማናቸውም የጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች እዳዎች የሌለበት መሆኑን፣
2) ግብር ከፋዩ በውዝፍ ግብር አከፋፈል ረገድ የገባው ስምምነት ስለመኖሩ፣
3) ግብር ከፋዩ በደረሰው/በተሰጠው የግብር ውሣኔ ላይ ለመስሪያ ቤቱ አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ ስለማቅረቡ፣ ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ወይም ለፍርድ ቤት ይግባኝ ስለማቅረቡ፣
4) ግብር ከፋዩ በግብር አወሳሰንም ሆነ በውዝፍ ግብር አከፋፈል ላይ ለባለሥልጣኑ አቤቱታ አቅርቦ አስተዳደራዊ ውሣኔ የሚጠብቅ ስለመሆኑ፣
5) ግብር ከፋዩ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የደረሰበት መሆን ስለመሆኑ፣

## 7. የምስክር ወረቀት የሚያገለግልበት ጊዜ ገደብ እና የምስክር ወረቀት ፎርሞች

የተሰጠ የምስክር ወረቀት ከዚህ በታች ለተመለከተው ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

1) ለጨረታ መሳተፍ የሚሰጥ ምስክር ወረቀት ደብዳቤው ከተፃፈበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 6 ወር ድረስ ብቻ፣
2) የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት፣
   - ሀ/ በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ሂሣባቸውን ለሚዘጉ እስከ ሰኔ 30 ድረስ፣
   - ለ/ በአውሮፓውያን አቆጣጠር ሂሣባቸውን ለሚዘጉ እስከ ታህሳስ 23 ድረስ፣

3) የምስክር ወረቀት ፎርሞች

ለጨረታ መሳተፍ፣ ለንግድ ፈቃድ እድሳት፣ ለተሸከርካሪ ከሳውዶ የሚያገለግሉ ናሙናዎች በአባሪነት ተያይዘዋል።

## 8. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተጀምረው የነበሩ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

## 9. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት እለት ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ 24/12 ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር

## አባሪ 1

**በጨረታ ለመሳተፍ፣ የንግድ ፍቃድ ለማሳደስ፣ የተሽከርካሪ ምርመራ ለማድረግ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት**

ቀን________________

ቁጥር______________

**ለሚመለከተው ሁሉ**

የ__________________________ ኃ/የተ/የግል ማኅበር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር____________ በጨረታ ለመሳተፍ/የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ/ የተሽከርካሪ ምርመራ/ከላውዶ ለማድረግ እንዲችሉ እስከ_________ ቀን ______ ዓ.ም. የሚያገለግል የምስክር ወረቀት /ክሊራንስ/ የተሰጠው/የተሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

## አባሪ 2

**ለንግድ ሥራ ማቋረጥ/ድርጅት ለመዝጋት/ የባለቤትነት ስም ለውጥ ለማድረግ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት**

ቀን________________

ቁጥር______________

ለ__________________________

**አዲስ አበባ**

የ____________________________ ኃ/የተ/የግል ማኅበር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር_______ የንግድ ሥራቸውን በከፊል /በሙሉ/ ስላቋረጡ/ የባለቤትነት ስም ለውጥ ስላደረጉ እስከ ___________ ቀን _____ ዓ.ም. የሚያገለግል የግብር አከፋፈል ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

# አባሪ 3

## የወጪ መጋራት ክፍያን በተመለከተ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት

ቀን__________________

ቁጥር__________________

### ለሚመለከተው ሁሉ

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ት__________________________________ የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት ክፍያ ሙሉ ለሙሉ የከፈሉ/ለመክፈል በቂ ዋስትና ያቀረቡ በመሆኑ ይህ የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶአቸዋል።

ከሠላምታ ጋር